

> " ETHIOPIA always has a special place in my imagination and the prospect of visiting Ethiopia attracted me more strongly than a trip to France, England, and America combined. I felt I would be visiting my own genesis, unearthing the roots of what made me an African. "
>
> Nelson Mandela

**Nelson Mandela: Long Walk to Freedom**

*በፍቅር ለይኩን (South Africa-Cape Town)*

የነፃነት አርበኛ፣የይቅርታ አባት፣ የፍቅር ተምሳሌት፣የአይበገሬነትና የፅኑ መንፈስ ባለቤት፣ የመለያየትንና የዘረኝነትን ፅኑ ግንብ በማይለወጥ ፍቅር ያፈረሱ፣ የሠላም መልዕክተኛ፣ የሰው ልጆች ሁሉ የአንድነት ምልክት ... ወዘተ በሚሉ ቅጥያ ስሞች በሚታወቁት በዛሬው የ92 ዓመት አዛውንት ኔልሰን ማንዴላ የትግልና የፓለቲካ ሕይወት ውስጥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ያላት ስፍራ በእጅጉ የተለየ ነው። የእናት ምድራችን የረዥም ዘመን የነፃነት ታሪክ በአንድ ወቅት በዚሁ በደቡብ አፍሪካውያን መራር የነፃነት የትግል ታሪክ ውስጥ በጉልህ የሚወሳ ለጥቁር ሕዝቦች የኢትዮጵያ አንፀባራቂ የነፃነት ታሪክ የሞራልና የወኔ ስንቅ ሆኗቸው እንደ መርግ የከበደ የአፖርታይድን የዘረኝነት አገዛዝ ከጫንቃቸው ለመጣል የዛሬይቱ ተመጽዋች ድሀ የራብና የጦርነት ምድር ተብላ የምትጠራው ምስኪኗ ኢትዮጵያ በትላንቱ ረዥም የጥቁር ሕዝብ እልህ አስጨራሽ የፀረ-ቀኝ ግዛትና የፀረ-ባርነት ትግል ውስጥ ትልቅ ተምሳሌት ነበረች።

አገራችን ከረዥም፣ ውጣ ውረድ ከበዛው፣ ብዙ ችግርና ፈተና ከሞላው ታሪካችን በእነዚህም ታሪኮች ውስጥ የቀደሙት ትውልዶች ካሳዩት ጀግንነትና ከከፈሉት መስዋዕትነት ጋር በማይመጥን የእውቀትና የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ መገኘታችን

የሚያንገበግበን ኢትዮጵያውያን ሁሉ የዘመናችን እውነታ ማለፍ የማንችለውን ጥያቄ ከፊታችን አምጥቶ ደንቅሮታል:: የድህነት፣ የበሽታ፣ የድንቁርና፣ የስደትና የውርደት ሕይወታችን እኛ ብቻ ሳንሆን ዓለም በሙሉ የሚያውቀው ሃቅ ከሆነ ሰንብቷል:: በዓለም ዙሪያ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከታሪካዊ ገናናነትና ክብር ተገንጥሎ የድህነት፣ የራብ፣ የጦርነት፣ የስደትና የውርደት ምልክት ከሆነ በርካታ ዓመታት ተቆጥርዋል:: ይሄን እንደ እግር እሳት እየለበለበ መቆሚያ መቀመጫ ያሳጣንን የእኛነታችን አሳፋሪ መለያ፣የተዥጐረጐረ ባለ መንታ መልክ ታሪካችን ትላንት ብቻ ሳይሆን ዛሬም አብሮን ቀጥሏል:: ይሄን የብዙ ትውልዶችን ጥያቄዎችንና በርካታ እንቆቅልሾችን የተሸከመውን የትናንት ታሪካችንን ዛሬ እየመረረንም ቢሆን የምንጋፈጠው፤ የምንገኝበት የዛሬ እውነታ ብዙዎቻችንን መንታ መንገድ ላይ ያቆመን ይመስለኛል:: ምክንያቱም የትናንትናዋን ኢትዮጵያን ክብር፣ ገናና ስልጣኔና ስም ዛሬ ልንደግመው አቅቶናልና!!!

ለዚህ ቁጭት ሀፍረትና እልህ ለተቀላቀለበት ጽሁፍ መነሻ የሆነኝ ከላይ በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኩት በእውቁ የነፃነት ታጋይ በኔልሰን ማንዴላ በራሳቸው የተዘጋጀው (Long Walk to Freedom) የተባለው መራር፣ እልህ አስጨራሽ፣ የፅኑ መንፈስ ባለቤት ያደረጋቸው የ27 ዓመቱ መራር የነፃነት ትግል ህይወታቸው የተተረከበት መጽሃፋቸው ነው:: ለዚህ መጽሐፍ መታተም የመጽሃፉ ባለቤት ራሳቸው ኔልሰን ማንዴላና የቅርብ የትግል አጋሮቻቸው የከፈሉት መስዋዕትነት፣ ዛሬ በሮቢን ደሴት ባሉት የትግል አጋሮቻቸው ሲተርክ የሰው ልጅ ለማንነቱ፣ ለታሪኩና ለነፃነቱ ያለውን ቃላት ሊገልጸው የማይችለውን ክብር በእጅጉ ያጐላዋል:: በነዛ የ27 ዓመታት የጭንቅና የመከራ ዘመን ማንዴላና የትግል አጋሮቻቸው እንዲሁም አንጋፋው የ (ANC) ፓርቲያቸው ለሰው ልጆች ነፃነትና እኩልነት የከፈሉትን ውድ መስዋዕትነት የሚተርከው መጽሐፍ ህያው ሆኖ ለዓለም ህዝብ እንዲበቃ የተደረገበት ሂደት፣ ብልሃትና ትግል በእጅጉ የሚገርም ነው:: ልዩ የሆነ የቀንና የሌሊት ጥብቅ ቁጥር በሚደረግበት የማንዴላ እስር ቤት ክልል *(Maximum Security Zone)* ኔልሰን ማንዴላ የራሳቸውንና የሕዝባቸውን የነፃነት ትግል ረዥም ውጣ ውረድ በየቀኑ በማስታወሻቸው እያሰፈሩ በልዩ ምስጢርና ብልሃት ወደ ውጭ እንዲወጣ በማድረግ፣ በሌላ ጊዜ ቁጥጥሩና ክትትሉ የማያፈናፍን ሆኖ ሲያገኙት ደግሞ የዕለት ተዕለት የፖለቲካ ትግል ሕይወታቸውንና የትግል አጋሮቻቸውን ደማቅ ታሪክ በማስታወሻቸው እያሰፈሩ በእስር ቤታቸው ፊት ለፊት ባለው የራሳቸው አትክልት ቦታ በልዩ ጥንቃቄ በመቅበር አንድ ቀን ይሄን የሰዉ ልጆችን አይበገሬነትና ለነፃነት ያለውን ውድ ክብር የሚያንጸባርቅ ታሪክ ህያው ሆኖ ሁሉም ሰው ያነበዋል በማለት ፅኑ ተስፋ ነበር **የዛሬው** (Long Walk to Freedom) መጽሐፍ ፅንሰትና ውልደት::

ገና በእናት ምድሬ በኢትዮጵያ ሳለው በደቡብ አፍሪካ በሚገኝ ዩኒቨርስቲ በሮቢን ደሴት ሙዚየም ገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠውን ነፃ (Scholarship) የትምህርት ዕድል ማግኘቴ ሲነገረኝ ከተሰማኝ ደስታ ባሻገር እጅግ ልዩ ስሜት ያጫረብኝ የሰው ልጅ የአይበገሬነት፣ የፅኑ መንፈስና የነፃነት ተምሳሌት በሆነችው በሮቢን ደሴት በአካል የመገኘቴ እውነታ በዓይነ ህሊናዬ ሲታየኝ የተሰማኝ ድብልቅልቅ ስሜት በቃላት ከምገልጸው በላይ ነው:: የበርካታ ዘመናት የጥቁር ህዝብ የነፃነት ተጋድሎ የጥቁር ህዝብ ውርደትና መከራ የተከተበበት ረዥሙ የአፍሪካ የጨለማው ዘመኗ እንደ መርግ የከበደው ታሪኳ፤ ሰው የመሆን ክብር፣ የኀሊና ነፃነት የማይገባቸው ለዘመናት የዘረኝነት መርዝ የተጣባቸው በዚህም መርዘኛ ስብከታቸው የሰውን ኀሊና ደጋግመው ያደሙ የታሪክ ጉዶች፣ ታሪክ በማይደብዝዝ ህያው ቀለም የከተበው የጥቁር ህዝብ የመውደቅና የመነሳት ታሪክ በኀሊና ሲታሰብ በቁጭትና በእልህ ኀሊና ይደክማል ልብም ይታመማል::

በተፈጠሩበት ምድር የመኖር መብት ተነፍጉአቸው፣ ሰብአዊ ክብራቸው ተደፍሮ፣ ነፃነታቸው ተረግጦ፣ ኀሊናቸው በዘረኞች መርዘኛ ስብከት ሲቆስል፣ የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው በጨካኞች እጅ ወድቃ፣ ጥቁር ሆኖ መፈጠር እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ክቡር የሰው ልጅ እንደ ዕቃ ሲሸጥና ሲለወጥ፣ ሰው የመሆን ክብራቸው ለማመን እስኪያዳግት እጅግ ተዋርዶ... አፍሪካ ያሳለፈችው መራር ጉዞ የልጆቿ ዕንባና ስቃይ ዛሬም በቅጡ ያልታበሰላት የእንቆቅልሽ ምድር ናት አህጉራችን አፍሪካ!

በአንፃሩ ይሄን የመከራና የውርደት ዘመን በአይበገሬነትና በፅኑ መንፈስ፣ በትግስት ፊት ለፊት ተጋፍጠው ለህዝባቸው ነፃነትን ጉህ ለማሳየት በነፍሳቸው የተወራረዱትን፤ ብርቅዬ የጥቁር ህዝቦች ፈርጥ፣ የፖለቲካና የነፃነት ትግል ማዕከል በአካል ለማየት መታደል ለዘመናት ስለ ረዥሙ ዘመን የአገሩ የነፃነት ታሪክ ሲተረክለት ላደገ፣ የአባቶቹ ጀግንነት፣ የሕዝቡ ኩሩ መንፈስ ክብር ለሆነው ኢትዮጵያዊ ልዩ ስሜትን የሚያጭር ነው::

የዚሁ የአህጉራችን የነፃነት ተጋድሎ የታሪክ አንብርት የሆነችው የሮቢን ደሴት በተጓዦች፣ በአሳሾችና በታሪክ ጸሃፍት የተዘገበ የ500 ዓመት የዳጉሰ ታሪክን በውስጧ የተሸከመች ናት:: ከዚህ በዘመናት ከዳጉሰ ታሪኳ ትልቁን ስፍራ የያዘው ከ1960ዎቹ ደቡብ አፍሪካ ነጻነቷን ስከተጐናፀፈችበት ያለው መራር የፀረ ቀኝ-ግዛትና የፀረ-አፖርታይድ ትግል ዘመን ዋንኛው የደሴቲቷ የታሪክ አንጓ ለዛሬው *(Rainbow Nation)* በሚል ቅፅል ለምትታወቀው ደቡብ አፍሪካ ደግሞ ዋና የፖለቲካ፣ የታሪክ፣ የባህልና የቅርስ ማዕከል ናት የሮቢን ደሴት:: ቀዝቃዛውን የአትላንቲክ ውቅያኖስን በማቋረጥ ከ 30-45 ደቂቃ ከሚፈጅ የመርከብ ጉዞ በኋላ የምትገኘው የሮቢን ደሴት ተፈጥሮአዊ

ውበት ልዩ ትንግርት አለው፣ በዚህች አጭር ፅሁፍ ስለ ሮቢን ደሴት ተፈጥሮአዊ ውበትና የዘመናት ታሪክ ለመተረክ የሚሞከር አይደለም፣ ምናልባት በሌላ ጊዜ እመለስበት ይሆናል፤ ከተነሳሁበት ብዙም ሳልርቅ በሮቢን ደሴትና በዩኒቨርስቲው የትምህርት ጊዜ ቆይታዬ ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝን አጋጣሚ ወደፈጠረው የጽሁፌ ዋና ጨብጥ ላምራ።

*በደቡብ አፍሪካ ረዥም የፀረ-አፖርታይድ ትግል በተለይም ደግሞ ከኔልሰን ማንዴላ መራር የነጻነት ትግል ሕይወት ጋር አገራችን ኢትዮጵያ ያላት ቁርኝት በእጅጉ የጠበቀ ነው። የነፃነት ትግሉ በተፋፋመበት በ1960ዎቹ በቅኝ ግዛት ስር ለሚማቅቁ በርካታ የአፍሪቃ አገሮች፣ለካሪቢያንና ለአፍሪካ አሜሪካውያን ጥቁር ህዝቦች ኢትዮጵያ እንደ ከነዓን በሩቅ፣ በተስፋና በናፍቆት ዕንባ የሚያስቧት የጥቁር ሕዝብ ነፃነትና የአይበገሬነት ተምሳሌት ሀገር ነበረች።* በአንድ ምሽት በሮቢን ደሴት ላይ በሚገኘው የመኖሪያ ቤቱ የትምህርት ክፍላችን አስተባባሪ *(Coordinator)* የራት ግብዣ አድርጐልን ይሄን የኢትዮጵያን የነጻነት ክብርና የሕዝቦቿን ኩራት፣ማንዴላ ለወታደራዊ ስልጠና ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በነበረበት ጊዜ (Long Walk to Freedom) በሚለው በራሳቸው በተዘጋጀው መጽሐፍ ላይ ስለ ኢትዮጵያ ቆይታቸዉ በተረኩበት የመጽሃፍ ክፍል ውስጥ ከራት በኋላ በሳሎኑ ከነበረው የመጽሃፍ መደርደሪያ መጽሃፉን በመውሰድ አብረውኝ ከነበሩ የክፍል ጓደኞቼ ጋር ስለ አፍሪካ የነጻነት ትግልና ኢትዮጵያ ስንነጋገር ከናሚቢያ የመጣች ጓደኛችን በሌላ የማንዴላ የሕይወት ታሪክ በሚተርክ መጽፍ ውስጥ ማንዴላ ወደ ኢትዮጵያ በገባበት ጊዜ የተጠቀመበትን በመጽሃፉ በአባሪነት አብሮ የተካተተውን የማንዴላን የኢትዮጵያ ፖስፓርት ስታሳየን ለውይይታችን ሌላ ተጨማሪ መረጃ ሆኖን ስንጨዋወት ሳለን፣ ይህችው የክፍል ጓደኛ ዬ በሃገሬ የረዥም ዘመን የነጻነት ታሪክና ተጋድሎ የተሰማኝን ደስታና ኩራት ገና ማጣጣም ሳልጀምር፣ *"... ግን ከዚህ አኩሪ ታሪካቹሁ ባሻገር ረሃቡና ጦርነቱ በአገራችሁ እንዴት ነው? በእውነት ነው የምልህ አገራችሁን ደጋግሞ ስላጠቃው ረሃብ ድርቅና የእርስ በርስ ጦነት* (*Civil Wars*) *የBBC ቴሌቪዥን ያቀረበውን ኘ ሮግራም ደጋግሜ አይቼዋለሁ፣ በእጅጉ የሚያሳዝን ነው የሚገርምህ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአገራችን ሰው ያለ አግባብ የተረፈውን ምግብ ሲጥል በረሃብ እያለቁ ያሉትን ኢትዮጵያውያን ሕዝቦች አስቧቸው..."* እንደሚባል አያዘነች ስትነግረኝ፣ ስሜቴ በእጅጉ ዳምኖ ውስጤ እያነባ በዛች ቅጽበት በጎሊናዬ አገሬ ያለፈችበትን ረዥም የመውደቅና የመነሳት ታሪክ እያመላለስኩ እኛ ብቻ ሳንሆን አፍሪካወያን ሁሉ የሚኩሩበት የረዥም ዘመን የነጻነት ተጋድሎ ታሪካንችንና የሕዝባችን ኩራት፤ ዛሬ በሄድንበት ሁሉ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከታሪካዊ ገናናነትና ክብር ተገንጥሎ የድህነት፣ የረሃብ፣ የጦርነት፣ የስደትና የውርደት ምልክት መሆኑን፤ በዚሁ በደቡብ አፍሪካ ቆይታዬም ባለሁበት ዩኒቨርስቲ ካገኘኋቸው ከተለያየ ዓለም የመጡ ተማሪዎችና ከዩኒቨርስቲው ውጭም በተለያየ አጋጣሚ ያገኘኋቸው ሰዎች ስለ አገራችን አንድም ምንም ጥሩነ ገር አያውቁም፣ የሚያውቁትም የሚበዙት የጦርነት የረሃብ ምድር መሆኗን ነው።

አንዲህ የዓለም ሁሉ መሳለቂያ ሆነን በሄድንበት ምድር ሁሉ የረሃብና የጦርነት ተምሳሌት ሆነን ታሪካችንና ክብራችን ተዋርዶ አገር እንደ ሌለን ተንከራታች፤ በስደትና በጉስቁልና በታላቅ መንፈሳዊ ስብራት ውስጥ ላለችው ለእናት ምድራችን ኢትዮጵያ እንደ ነቢዩ ኤርምያስ እንባውን እያፈሰሰ ከሕያው የአብርሃም የይስሃቅና የያዕቆብ አምላክ ጋር የሚሟገትላት ማን ይሆን እንዲህ ያለ፦

*"... አቤቱ የሆነብንን አስብ ፣ ተመልከት ስድባችንንም እይ።*
*ርስታችን ለእንግዶች ቤቶቻችንም ለሌሎች ሆኑ፣*

*ድሀ አደጐችና አባት የሌለን ሆነናል*
*እናቶቻችን እንደ መበለቶች ሆነዋል …*
*ስለምንስ ለረጅም ዘመን ትተወናለህ?*
*አቤቱ ወደአንተ መልሰን እኛም እንመለሳለን*
*ዘመናችንን እንደ ቀደሞ አደስ ::"*

*(ሰቆቃወ ኤርምያስ ፭÷፩)*

ለዘመኑ ኤርምያሶች ለተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆቹ የሙሾ ወራት ነው:: የተሰባበሩ ቃል ኪዳኖች፣ ብሔራዊ ውርደት፣ የህዝብ እልቂት፣ረሃብና ጦርነት የትናንት የቅርብ ታሪካችን አካል ነበሩ፣ ዛሬም አብረውን አሉ:: ተስፋን ሰንቀን ጉልበቴ በርታ በርታ ባልንበት የተስፋ ጭላንጭል ዘመን እንኳ ወደፊት እንዳንራመድ በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና፣ ማኅበራዊ ቀውሶቸ እያደናቀፉን ጉዞአቸን የዔሊ ጉዞ ሆኖአል:: ይህ ፁሁፍ በርግጥ ላለፍንበት ረዥም የመውደቅና የመነሳት ታሪክ ላጋጠመን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውስ፣ ውድቀትና ድቀት ታሪከዊ ትንታኔ ለመስጠት አይደለም:: የዚህ ፀሁፍ ባለቤትም በዚህ አጭር ፁሁፍ ይህን ለማድረግ ይቻላል የሚል ቅዠት የለውም:: ይህን ሰፊ ርዕሰ-ጉዳይ በመጠኑም ቢሆን ለመረዳት የሚፈልግ በአገራችንም ሆነ በውጭ አገር ፀሐፍትና ምሁራን የተጻፉ መጽሐፎችን፣ ጥናታዊ ጽሁፎችንና መዛግብትን በማገላበጥ ማንኛውም ግለሰብ የራሱን ግንዛቤና የኀሊና ፍርድ መስጠት እንደሚችል በመጠቆም፣ለዚህ ጽሁፍ አንባቢዎች እና ለራሴ አንድ ጥያቄ ማቅረብ እፈልጋለሁ::

ይኸውም በኢትዮጵያ የረዥም ዘመን ታሪክ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ያላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በረዥም ዘመን ታሪኳ በአገራችን ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ፣ፖለቲካና ማኅበራዊ ተቋማት ውስጥ የነበራት መልካም ገጽታና በጐ ድርሻ ዛሬ የደበዘዘበት ምክንያት ምንድን ነው? ***በዘመናችን ያሉ የሃይማኖት አባቶቻችንስ ቤተክርስቲያናችን ለምድራችን መፍትሄና መድኃኒት አምጪ ይሆናሉ ብለን ስንጠብቅ ለምን ልባችንን አደሙት? የፍቅር ተምሳሌት፣ የአንድነት አርማ፣ የእውነት ጠበቃ፣ በእጃቸው በጨበጡት በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀሉ ደም የመለያየትንና የዘረኝነትን የኢያሪኮ ግንብ የሚያፈርሱ ብለን ተስፋ አድርገናቸው ስንጠብቅ ምነው ተስፋችን ሁሉ እንደ እንቧይ ካብ እንዲሆን አደረጉት? መንጋዎቹስ ስለምን ለተኩላ እራት ይሆኑ ዘንድ ተዋቸው?***

ይህ ጽሁፍ በምንም ሁኔታ ቢሆን እግዚአብሔር አክብሮ በሾማቸው አባቶቻችን ላይ የስድብንና የፍርድን ቃል ለማምጣት የጻፍኩት ጽሁፍ እንዳልሆነ አንባቢ በጥብቅ እንዲገነዘብልኝ እፈልጋለሁ፣ አንዳንዶቹ ጸሐፊዎች በማያውቁትና ባልገባቸው ነገር ውስጥ እየገቡ ባልተሰጣቸው ስልጣን በቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ላይ የስድብና የፍርድ ቃል ከሚናገሩ ግለሰቦች ጋር መቼም መቼም ቢሆን ብዕሬ ከነሱ ጽዋ አትካፈልም:: ወይም ደግሞ እንዳንዶቹ የዋኅን መለኮታዊ ቃና ያለዉ በሚመስል አካሄድ

የሰሜቱን ከምድሩ እያደባለቁ ዞሮ ዞሮ አንተ/ አንቺ/ እና ሚድረግ ምንችለዉ ነገር የለም ወይም ጥቂት ነዉ መፍትሄዉ በእኛ እጅ አይደለም በሚል ስለችግሮቻችን እንዳነጋገርና እንዳንወያይ ከሚከብቡ ሰዎች ጎራም አይደደለሁም:: በአንፃሩ ግን ዛሬ ቤተክርስቲያናችን ያለችበትንና የገባችበትን ውሉ የጠፋ የሚመስል የተወሳሰበ ችግርና ፈተና፣ በእናት ቤተክርስቲያናቸው ፍቅር፣ የቅንአት እሳት እየነደዱ ቤተክርስቲያናችን ፍፁምና ምሉዕ ወደሆነው የክርስቶስ ሙላት መልክ እንድትደርስ በንፁህ ኅሊና እና በቅንነት መንፈስ ከሚመክሩ፣ ከሚጽፉና በፀሎት ከሚተጉ ኢትዮጵያን ጋር ሁሉ አብሬ የምቆም በብዕሬም ይሄን የማፀና መሆኔን የዚህ ጽሁፍ አንባቢዎች አንዲያውቁልኝ አደራ እላለሁ:: ይሄን ካልኩ በኋላ ግን ከጠዋት እስከ ማታ፣ ከሳምንት እስከ ሳምንት ከወር እስከ ወር፣ ከአመት እስከ አመት፣ ቅዳሴው፣ ማኅሌቱ፣ሰአታቱ በማያቋርጥበት፣ ምልጃው፣ምስጋናው፣ ጸሎቱና ጾሙ በሚታወጅበት አውደ ምህረት ቢያንስ ለሌሎች ባይተርፍ ለራሳችን የሚሆን ሰላምና ፍቅር ልናጣበት የቻልንበት ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሁሉን በሚያይና በሚሰማ ዓይኖቹ በምድር ዙሪያ ሁሉ በሆኑ በአምላክ ፊት ነጋ ጠባ እየጮኽን እንባችን እንደ ራሄል እንባ ከጸባኦት መንበር ያልደረሰበት ለቅሶአችንና ጩኸታችን ያለያየንና የከፋፈለንን የኢያሪኮ ግንብ ለማፍረስ አቅም ያጣበትን ምክንያቱን እኔም እናንተም ራሳችንን መጠየቅ ካለንበት የታሪክ ምዕራፍ ላይ የደረስን ይመስለኛል:: ነቢዩ ኤርምያስ በታላቅመፃፈሳዊ ስብራትናጉስቁልና ለነበረችዉ ኢየሩሳሌም የጮኸው ጩኸትና ለቅሶ ህዝባችን ቤተክርስቲያናችንና እኛ ላለንበት ምስቅልቅል የሚ ስማማ ይመስለኛል፦

*"... ኢትዮጵያ ሆይ ምን እመሰክርልሻለሁ፣ በምንስ እመስልሻለሁ?*
*ስብራትሽ እንደ ባህር ታላቅ ነውና፣ የሚፈውስሽ ማን ነው?*
*ነቢያቶችሽ ከንቱና ሃሰተኛ ራዕይ አይተውልሻል፣ ምርኮሽንም*
*ይመልሱ ዘንድ በደልሽንም አልገለጡም:: ከንቱና የማይረባ*
*ነገር አይተውልሻል:: መንገድ አላፊዎች ሁሉ እጃቸውን ያጨ*
*በጭቡብሻልና፣ በውኑ የውበት ፍጻሜ፣ የእግዚአብሔር ሃገር፣*
*የክርስቲያን ደሴት፣ የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት አርማ፣ የአፍሪካ*
*መዲና፣ የሕዝቦች ደስታ የሚሏት ሃገር ይህች ናት እያሉ..."*

*(ሰቆቃወ ኤርምያስ ፪፥፲፫)*

የአገራችንም ሆነ የቤተክርስቲያናችን ስምና ክብር ከፍ ከፍ እንዲል ለዘመናት የተጣባን የረሃብና የጦርነት ታሪካችን እንዲለወጥ የቤተክርስቲያን፣ የአባቶችና የእኛ ኃላፊነት ምን ድረስ ነው? ***ብዙ ጊዜ ያለመታደል ሆኖ ምድራችን ባለ ራዕይ የማይፈጠርባት ቢፈጠርም የሚጨንግፍባት የፍቅርና የእምነት አርበኞች ረሃብተኛ ከሆነች ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል::*** ለዚህ ጽሁፌ መነሻ የሆነኝ የኔልሰን ማንዴላ በራሳቸው የተዘጋጀው (Long Walk to Freedom) በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ እሳቸውና የትግል አጋሮቻቸው የከፈሉት መስዋዕትነት ለበርካታ ዓመታት ለህዝባቸውና ለአገራቸው ነፃነት ያፈሰሱት የተስፋ እንባና ደም ዛሬ ደቡብ አፍሪካ ተረጋግታ እንደ አገር ለመቀጠል በዋነኝነት የሚጠቀስ ነው::

የዛሬው 92 ዓመት አዛውንት ማንዴላ እጅግ ከባድ መራርና በእጅጉ ትዕግስትን ከሚፈታተነው የ27 ዓመታት የሮቢን ደሴት እሥራት ዘመን በኋላ ለነፃነት ሲበቁ መጀመሪያ ያከናወኑት ነገር ቢኖር ህዝባቸውን ለበርካታ ዓመታት ለሞት፣ ለውርደትና ለሰቆቃ ከዳረገው የአፓርታይድ ዘረኛና ከፋፋይ መንግሥት መስራችና አቀንቃኝ ወደነበሩት የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ሟች ኘሬዚዳንት ሚስት ዘንድ በመሄድ በቀድሞ በአፖርታይድ ዘመን አሁን በሕይወት የሌሉት ባለቤታቸው በሳቸውና በህዝባቸው ላይ ስላደረሱባቸው ታሪክ ለማይረሳው ግፍና መከራ ከልብ የሆነ ይቅርታ ማድረጋቸውን በአካል በሟች ኘሬዚዳንት ቤት ተገኝተው ለባለቤታቸው፣ ለህዝባቸውና ለዓለም ህዝብ ሁሉ ባወጁበት ጊዜ መላው ዓለም በአንድ ድምጽ ለዚህ ከንፁህ ፍቅር ለመነጨ የኔልሰን ማንዴላ የይቅርታ መልዕክት ብራቮ ማንዴላ! ምድራችን ፍቅርንና ይቅርታን የሚያውጁ እልፍ ማንዴላዎች ያስፈልጓታል በማለት ይሄን የብዙዎችን ልብ የነካ ታላቅ ዜና በዓለም ሁሉ አዳረሱት:: የደቡብ አፍሪካ ህዝብም ከዚህ የማንዴላ ርምጃ በኋላ ነው ልቡን ለይቅርታና ለምህረት ክፍት በማድረግ የዘር መድሎ የሌለባትን አዲሲቷን ደቡብ አፍሪካ ለመገንባት እጅ ለእጅ ለመያያዝ ቃል ኪዳን የገቡት::

በወቅቱ በእጅጉ ተፈርቶ የነበረዉ ለዘመናት በጥቁር ደቡብ አፍሪካውያን ህዝቦች ላይ ነጮች ባደረሰቡት ግፍ ኀሊናው የቆሰለ ህብረተሰብ ይወስደዋል የተባለው የበቀል እርምጃ እንደተፈራው ሳይሆን ቀርቶ ዛሬ አገሪቷ *(Rainbow Nation)* እንድትባል ያደረጋት ነጩ፣ጥቁሩ፣ኤዥያው፣ህንዱ በአጠቃላይ የዓለም ህዝብ ሁሉ አንፃራዊ በሆነ በሠላም የሚኖርባት አገር ለመሆን በቅታለች:: ለዚህ አንፃራዊ የአገሪቷ ሠላምና መረጋጋት የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱት ታላቁ የነፃነት አርበኛ የዛሬው የ92 ዓመት ዕድሜ አዛውንት ማንዴላ ናቸው::

የማንዴላ የፍቅርና የይቅርታ ስብከት በዚህ ብቻ አልተገታም ከ27 ዓመታት አስጨናቂና መራር የእሥር ቤት ሕይወት ነፃ ወጥተው የመጀመሪያው የነጻይቷ የደቡብ አፍሪካ ጥቁር ኘሬዚደንት ሆነው ሲመረጡም ለህዝባቸውና ለዓለም ሁሉ ሕዝብ ባደረጉት ንግግር እንዲህ ነበር ያሉት፦

> *"...ዛሬ አሉ እኚያ ታላቅ የነፃነት አርበኛና የሠላም መልዕክተኛ እንባና ሳግ በተቀላቀለበት ድምፃቸው ዛሬ ነጮች ወንድሞቻችን ላደረሱብን የሰው ልጅ ኀሊና ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ለሆነው ውርደት፣መከራ፣ግፍና ሞት በቀልን የምናውጅበት ቀን ሳይሆን የአፖርታይድን ዘረኛና ከፋፋይ የታሪክ ምዕራፍ ዘግተን ነጭ፣ጥቁር ሳንል በአንድነት ተባብረን አዲሲቷን ደቡብ አፍሪካን ለመገንባት እጅ ለእጅ የምንያያዝበት ብሩህ ዘመን፣ አዲስ የታሪክ መክፈቻ ቀን ነው :: ... ቂም ይቅር፣ ለበቀል የተነሱ ሰይፎች ወደ ሰገባቸው ይመለሱ . . . ምድራችንን ሰላም፣ ፍቅርና*

*ምህረት የሚታወጅባት ትሁን . . . እግዚአብሔር አፍሪካን ይባርክ!"*

ይህ አፍሪካውያንን ብቻ ሳይሆን መላው ዓለምን ያስደመመው የኔልሰን ማንዴላ የሠላምና የይቅርታ መልዕክት በመገናኛ ብዙኃን ወደ ጆሮአቸው የደረሰ ሁሉ ከአፍሪካውያን ጋር አብረው በደስታ በፍቅር ስለፍቅር አንብተዋል። በዚህ የይቅርታና የፍቅር መንፈስ ከአፓርታይድ መንግስት ለውጥ በኋላ በደቡብ አፍሪካ የተቋቋመው የእውነት አፈላላጊና የእርቅ ኮሚሽን *(Truth and Reconciliation Commission)* በአገሪቷ መፃዒ ታሪክ ላይ ታላቅ የሆነ የፍቅርና የይቅርታ አሻራ ጥሎ አልፏል። በዓለም አቀፉ የሠላም ኖቤል ተሸላሚ በሆኑት በደቡብ አፍሪካዊው ሊቀ ጳጳስና የነፃነት ታጋይ አቡነ ዴዝሞን ቱቱ እና ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በተውጣጡ የሕግ ባለሙያዎች፣የሃይማኖት አባቶች፣ የሰብዓዊ መብት ታጋዮች፣ የታሪክ ተመራማሪዎች፣ የፖለቲካ ተንታኞች፣ የዘረኛው የአፓርታይድ መንግስት ሰለባዎች የተቋቋመው ይሄ የእርቅ ኮሚሽን ባዘጋጃቸው ችሎቶች የሰው ልጅ በመሰሉ ላይ እንዲህ መጨከን ይቻለዋል እስኪባል ድረስ ለመስማት የሚዘገንኑ የትናንትናዋ የደቡብ አፍሪካ ጥቁር ህዝብ ግፍና መከራ በሰፊው ችሎት በዕንባና በሲቃ ታጅቦ ተሰምቷል። ብዙዎች በዕንባ የተራጩበት፣በዳየና ተበዳይ ፊት ለፊት ሆነው ይቅር ለእግዚአብሔር የተባባሉበት፣ የፍቅር መልዕክቶች የተሰበኩበት የትናንት በደልና ኃጢአት በይቅርታ ዳግም እንዳይነሳ የተዘጋበት ችሎት የዛሬዋን ደቡብ አፍሪካ መልክ መቀየር የቻለ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፍቶ አልፏል።

በዚህ ኮሚሽን ችሎት ላይ የተከናወኑትን አስገራሚና ልብ የሚ ነኩ ክስተቶችና ትዕይንቶች በሌላ ጊዜ በሌላ ጽሁፍ በሰፊው የምመለስበት ይሆናል፣ በዚህ ጽሁፍ ስለ እርቅ ኮሚሽኑ በጨረፍታም ቢሆን ላነሳ የወደድኩት፣ *ዛሬ ቤተክርስቲያናችን ካለችበትና ከተዘፈቀችበት የበቀል፣ የመለያየት፣ የዘረኝነትና የጎጥ መንፈስ ተላቃ የሠላም የፍቅርና የይቅርታ መልዕክት የሚታወጅባት እንድትሆን ቤተክርስቲያኒቷን የሚመሩ አባቶቻችን እንደ ማንዴላ፣ እንደነ አቡነ ዴዝሞን ቱቱ ያለ ታላቅ የታሪክ ኃላፊነት የሚወስዱት መቼና እንዴት ነው?* የዘመናችን እውነታ ማለፍ የማንችለውን ጥያቄ ከፊታችን አምጥቶ ደንቅሮታል። *ሠላምን፣ፍቅርንና ይቅርታን በመስበክ ወሳኝነት ያለውን ሚና መጫወት የሚገባት ቤተ ክርስቲያናችን በመለያየት፣ በዘረኝነትና በክፋት የተተበተበች ከሆነ መድረሻችን የት ነው? የህዝባችንና የቤተክርስቲያናችንስ ዕጣ ፈንታ ምን ይሆናል? መቼ ነው «ይሄን ሕዝብ በምድረበዳ ከምታጠፋው እኔን ከሕይወት መዝገብ ደምስሰኝ» የሚሉ ሙሴዎችን በቤተክርስቲያናችን ማየት የምንችለው? እንደ ነቢዩ ኤርምያስ በታላቅ ለቅሶ «አቤቱ የሆነብንን አስብ» በማለት ለሕዝባቸው የሚያነቡ የእግዚአብሔር ነቢያትንና ካህናትን በቤተክርስቲያን ዐውደ ምህረት ለማየት የምንታደለው?*

**የዚህ ፅሑፍ ፀሐፊ በጨለምተኝነት መንፈስ (*spirit of pessimism*) ቤተ ክርስቲያን ምንም ሰው እንደሌላት የምሟገት እንደ ዘመኑ የቀበሮ ባህታውያን ተስፋ የሚያስቆርጥ የመአት መልዕክትን ለማስተላለፍ ሳይሆን እርስ በርስ በመነጋገርና በመወያየት ለተሻለ ነገ ዛሬ ከአምላካችን የተሰጠን የመመለስ የይቅርታ ቀን መሆኑን ለማስረገጥ ነው። ዛሬም ለቤተክርስቲያናችን ትንሣዔ የሚተጉ፣በፀሎት የሚጋደሉ አባቶች እንዳሉ አምናለሁ። ከሁሉም በላይ የእረኞች አለቃ ለመንጋው በእጅጉ የሚራራ እስከ መስቀል ፍቅር ለወደዳት፣ደሙን ላፈሰሰላትና ነፍሱን ለሰጠላት ቤተ ክርስቲያን መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ለአፍታ እንኳ ቸል እንደማይላት አምናለሁ። በፍቅር ስለ ፍቅር እንነፍ ለይቅርታ ልባችን ክፍት ይሁን የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር አገራችንና ቤተክርስቲያናችንን ያስብልን!!!**

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**ሻሎም! ሠላም!**

***For any comments and suggestions you may reach me on fikirbefikir@gmail.com***